# በአንድነት ስም አንድነትን ለመግደል መዝመት

ከአህመድ ይማም

በኢትዮጵያ አንድነት ስም በተደራጁት እና እንገንጠል በሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ግልጽ የሥልት ልዩነት መስመር ነበር። በሀገር አንድነት ማመን አለማመን። በአንድነት የሚያምኑት ወገኖች ምንም ምንም የፖለቲካ አመለካከት ልዩነት ይኑራቸው በግልጽ የሚታይባቸው አንድ የጋራ ባህሪ ነበር - በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ሥር ይህ ይሁን፣ ያ ይሁን መባባል። ትላንትና የኢትዮጵያን ህጋዊ ድንበር ወሮ ስንት ጥፋት ያደረሰው የዚያድ ባሬ ጦር የባህር ሃይል መኮንን በነበረ ባዕድ የሚመራውን የኦጋዴን ብሄራዊ ነፃ አውጪ ግንባር (ኦብነግ) ጨምሮ እንገንጠል ባዮቹ ደግሞ በበኩላቸው "በኤርትራው ዓይነት ፌዘኛ ህዝበ-ውሳኔ ነፃነታችንን (በእኑሰ አባባል ከአብስኒያ ቅኝ አገዛዝ) ማግኘት አለብን ነበር የሚሉን። የተገለፀውን አቋማቸውን ግትር ብለው ፊት ለፊት ነበር የሚያራምዱት። ከሰሞኑ ግን ኢትዮጵያን ጭዳ በማድረግ፣ በቋንቋ መንደር ለተደራጁ ድርጅቶች ቅርጫ ለማከፋፈል እየተገበረ ያለው ሌላ ተጨማሪ ብልሃት <u>በአንድነት ስም አንድነትን ለመግደል መዝመት</u> ነው። ይህም ለዘመናት ባዕዳን፣ ወያኔም በ 1983 ዓ. ም. ኢትዮጵያን በወታደራዊ ሃይል ለመቆጣጠር ሥራ ላይ ካዋለው ስልት የተቀዳ ነው። መስሎ አስመስሎ፣ ከፍሎ ከፋፍሎ መቆጣጠር። ወያኔዎች በየቋንቋው ጠፍጥፈው በሰሯቸው አሻንጉሊቶች ታጅበው አዲስ አበባ የደረሱት፡

ወሎን — በዘመቻ ዋለልኝ
ጎንደርን — በዘመቻ ቴዎድሮስ
ወለጋን — በቢሊሱማ ወልቂጡማ (በነፃነትና እኩልነት ዘመቻ)

ወዘተ ማለስለሻ ሥልትም ጭምር ተሻግረው ነበር። ወያኔ በጠላትነት በሰየመው ወገን ላይ ከኮሶ የመረረ ጥላቻና አገዛዝ ሰንቆ "ቼ!" ፈረሴ እያለ መጋለቡን ቢያውቅም፣ ከየአካባቢዎቹ ጋር ትስስር ባላቸው ታሪካዊ ሰዎች ስም በመሰየም፣ ወይም ቋንቋን ተጠቅሞ እያማለለ አታሎ አልፏል። አጅበውት ከአራት ኪሎው ቤተመንግሥት ግቢ የደረሱት እንገንጠል ባዮቹም — እነ ኦነግ፣ ወዘተ፡

- ምንም እንኳ ጥቂት የሹመት ወንበር ተሰጥቷቸው፣ የዘረኛነት መርዛቸውን መርጫ የአጭር ጊዜ ሥልጣንና ዕድል ቢያገኙም፣
- ምንም እንኳ የኢትዮጵያዊነት ቅስም መስበሪያ፣ ተስፋ ማሳጫ እንዲሆን ታስቦ የተቀመመ አንቀጽ 39ን ዓይነት ብሄራዊ ህግ ሆኖ ቢወጣም

አልተሳካላቸውም። ወያኔ አገልግሎታችሁ አራት ኪሎ ቤተመንግሥት ድረስ አጅቦ ማድረስ ነው ብሎ ፊት ስለነሳቸው፣ በስሙ የሚነግዱበትም ሆነ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እምቢ አንድነቴን፣ ኢትዮጵያዊነቴን ስላላቸው። እዚህ ላይ አንድ ገጠመኝ መጥቀስ ተገቢ ይሆናል። ወያኔ አዲስ አበባን የተቆጣጠረ ሰሞን ነው። የኦነግ ካድሬዎች አዲስ አበባና ዙሪያው የሚኖሩ ኦሮምኛ ተናጋሪ ወገኖቻችንን በየቦታው እየሰበሰቡ የዘረኛነት መርዛቸውን ለመርጨት እና ለማነሳሳት የሚጥሩበት። አንድ ቀን ሱልልታ አካባቢ የሄደው የኦነግ ሹመኛ ሕዝቡን ሰብስቦ ብዙ ብዙ አለ። ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ኮንኖ፣ ለኦሮሞዎች ከመገንጠል በቀር ፍቱን መዲሃኒት እንደሌለ አስረግጦ ሲሰብክ ቆየ። ንግግሩን ጨርሶ ለተሰብሳቢዎቹ እድል ሲሰጥ አንድ በትዕግሥትና በትዝብት ሲያዳምጡ የነበሩ ጉምቱ አባት እጃቸውን አወጡ። ተነሱናም ወደፊት ቀረቡ። በጋቢያቸው ጫፍ የቋጠሩትን ፈቱና ያንን የኦነግ ሹመኛ እያሳዩ፣

"ለመሆኑ ይህንን በቀላሉ መለያየት ይቻልሀል የእኔ ልጅ?" ብለው ጠየቁት ጥርት ባለ ኦሮምኛ። በጋቢያቸው ጫፍ ቋጥረው የነበረው የተደባለቀ ቀይና ነጭ ጤፍ ነው።

"አልችልም" ሲላቸውም፤

“አየህ የእኔ ልጅ፣ እኛም እንደዚያው ተደባልቀናል፣ ተዋልደናል፣ ተጋብተናል። ማንን ከማን ተለያያላችሁ። ... " ብለው ነበር የመከሩት። ኦነግ እና መሰሎቹ ሰውን እስከ ሕይወቱ ገደል በመክተት፣ በር ዘግቶ በማቃጠል አሰቃቂ ጭፍጨፋ አከናውነው በሃይማኖት፣ በቋንቋ ለማናከስ ሲሞክሩም፣ በአባታዊ ምክክርና ተግሣፅ እሳቱን ያጠፉት ኦሮምኛ ተናጋሪ አባቶችም ጭምር ናቸው። እስከዛሬም ድረስ የዚያ ሹመኛ ዓይነት አጨራራሽ የዘር ቅስቀሳ እንደቀጠለ ቢሆንም ህዝቡ ግን አልተቀበለውም። ጥማቱ ዴሞክራሲ፣ እኩልነት የሰፈነበት አስተዳደር እንጂ የየጎጡ ፕሬዚዴንት፣ ሚኒስተር ስለመሆንን ለሚያልሙ ጥቂት ሰዎች በየቋንቋው ቅርጫ ገብቶ መበታተን እንዳልሆነ በቅርቡም እንኳ፣ በ1997 ምርጫ ወቅት በግለጽ አሳይቷል። በሥውርም በግልፅም ለዓመታት የተዘመተበት ኢትዮጵያዊነት ነበር ድል የተጎናፀፈው - በ1997 ሕዝባዊ አመጽ። ከአዜው አገዛዝ ጀምሮም በሚሊዮን የሚቆጠሩ የቋንቋ ልዩነት ሳይገድባቸው በአንዲት ኢትዮጵያ ጥላ ሥር የሥርዓት ለውጥ እንነዲመጣ በየሚያምኑባቸው ህብረ-ብሄራዊ ድርጅቶች ገብተው ታግለዋል፣ አየታገሉም ነው።

በዚህ ተቃራኒ ደግሞ ያን እምቢ አልሽነፍም ያለ ኢትዮጵያዊነት፣ ያንን የሕዝብ አንድነት የመሸርሸር ጥረቱ ቀጥሏል - በወያኔም፣ ወያኔን እቃወማለሁ በሚለው ፀረ-ኢትዮጵያው ሃይል በኩል። ከ1997 ወዲህ በተለይ ወያኔን ብቻ ሳይሆን አንድነትንም ተቃዋሚ ነን የሚሉት ሃይሎች ተጨማሪ ሥልት ቀይሰው የአፍቃሪ-ኢትዮጵያ ጎራውን ለመበታተንና ለመከፋፈል ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ነው። በአንድነት ስም አደራጅቶ አንድነትን መገዝገዝ። ብዙ ድረገፆች፣ ሬዲዮ ጣቢያዎች ገዙ - የኦነግን፣ ኦብነግን ወዘተ ገድል፣ ዓላማ የሚያወድሱ። አሁን ደግሞ ስለ<u>ኢትዮጵያ አንድነት መጨነቅ የለብንም</u> የሚሉ ሰዎች ሕብረ-ብሔር ነን በሚል ተደራጅተው በግልጽ በአደባባይ ወጥተዋል። መቼም እንኳን የሀገርን ህልውና ያህል የግል ሰራተኛም ሲቀጥሩ "ምን ትሰራ ነበር?’ ተብሎ ይጠየቃል እና የእነኝህን ሰዎች ያለፈ ታሪክ ለመረመረ በችኮላ እምነት የሚጣልባቸው አይደሉም። ካቋም አቋም መገለባበጥ፣ ከድርጅት ድርጅት መዝለል የለመደባቸው ናቸውና። በአጠቃላይ የሰሞኑን የተቃዋሚ ጎራ ሁኔታ ልብ ላለ ከትላንት ወዲያ ለአንዲት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ የታገለውን አንድ ትውልድ ክደው አለዚያም ከነበረው ወታደራዎ አገዛዝ ጋር አብረው ወይም ተማስለው የመተሩ እና ትላንት ደግሞ ከወያኔ ጋር አብረው የዛሬው መከራችንን ችግኝ ኮትኩተው ያሳደጉት ዛሬ ግንባር ፈጥረው፣ ሳንጃ ወድር ብለው ተነስተዋል — በኢትዮጵያ አንድነት ላይ።

ይህን ሀቅ በማስረጃ ላስረዳ። "ለመሆኑ ይህ ህብረ-ብሄር ነኝ የሚለው ድርጅት መሪዎች ባብዛኛው እነማን ናቸው?" ብለን እራሳችንን እንጠይቅ። ብርሃኑ ነጋ፣ አንዳርጋቸው ጽጌ፣ ኤፍሬም ሌጆቦ (በብእር ስም ኤፍሬም ማደቦ የሚባል) የሚጠቀሱ ናቸው። የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ሃገር ያወቃቸው፣ ፀሐይ የሞቃቸው የወያኔ አጃቢዎች ነበሩ አዲስ አበባ ሲገባ። በተለያየ መንገድም አገልግለውታል፣ ዛሬ መራር ፍሬውን አፍርቶ እየተጋትነው ያለውን መርዘኛ ኮሱ አታክለውታል። ወያኔ በኢትዮጵያ አንድነት አንደራደርም ብለው ቋራ ላይ ከገጠማቸው የወያኔ፣ የሻእቢያና የሱዳን የጋራ ሃይል ጋር በመፋለም በተሰውት የኢሕአፓ ጀግኖች፣ አናፈገፍግም ባሉት የኢትዮጵያ ጦር አባላት ሬሳ ላይ ተረማምዶ አዲስ አበባ ሲገባ እቅፍ አበባ ይዘው ነበር የተቀበሉት። በመሃል ሀገርም የህዝብ ልጆችን እያደነ ሲያጠፋ እነሱም በትብብር የፈፀሙትን ወንጀል ጊዜና ታሪክ ያወጣዋል። አንዳርጋቸው ስለአማርኛ ተናጋሪው የህብረተሰባችን ክፍል የፃፈው ከታሪክና ከሃቅ ጋር የተጣላ መፅሀፍ የግለሰቡን እውነተኛ አስተሳሰብ የሚያሳይ ይመስለኛል — ዓይናችንን ተጨፍነን እንሞኝ ካላልን በስተቀር። ያን መርዘኛ እና የኢትዮጵያ ግንባታ ያለፈበትን ሂደት ኮንኖ ለመግደል የከተበውን መጽሐፍም በመደረሱ ሲፀፀት አልሰማነውም። በሌላ በኩል የወያኔ አጃቢ አትሁን ሲባል ምክር ባለመስማቱ ሲፀፀት ተሰምቷል። ይህም የንስሃው አህዱ ሊሆን ይችላል። ባልደረባው ብርሀኑ ግን ከወያኔ ጋር ስለነበረው የአጋፋሪነት ትብብር አንዲትም የፀፀት ቃል ሲወጣው አልተሰማም። በእሥር ላይ እያለ የፃፈው ባለብዙ ገጽ መጽሐፍ፣ ባለቤቱ እሥር

ቤት እያለ ፀንሳ መውለዷ፣ ቀደም ሲል በህብረት ጥላ ሥር ይደረግ የነበረውን የተቃዋሚዎች ትብብር ለማዳከም ዓላማ ሌላ ቅንጅት በመፍጠር፣ በሁዋላም ይህንኑ የተፈጠረውን ቅንጅት ለመበታተን የተጫወተው ሚና፣ ብዙ ብዙ ጥያቄዎችን የሚያጭሩ፣ በይደር ታሪክ የሚፋረደው ጉዳዮች አሉ። አሁንም — ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል እንዲሉ ሆነና የእኛ ነገር — ወደሁዋላ እንደምመጣበት ዓይን ባወጣ ውሸት እሱና ባልደረቦቹ ሊያሳምኑን በመሞከር ላይ ናቸው — ስለ ኦነግ፣ ኦብነግ። የቋንቋ ክልልን ጥሶ በኢትዮጵያ አንድነት የሚያምነውን አዕላፍ ወገን ለማሳመን ያልተቻላቸው ግን የመሰባሰቢያ መርሁ አልፋና ኦሜጋ የሆነውን የሀገሩን ህልውና ለድርድር አሳልፎ ከሰጠ ምን ይዞ እንደሚቀር ነው። በሀገር ህልውና፣ በሀገር የመኖር አለመኖር ወሳኝ ጥያቄ ላይ በእነሱና በደጋፊዎቻቸው አባባል አክራሪነት ከተባለ፣ ለኢትዮጵያ ህልውና ሕይወታቸውን የሰጡት ቀደምት አዕላፍ እናት አባቶቻችንም አክራሪ ስለነበሩ ክብር ለእነሱ ክብር ለእኛም ልንላቸው ይገባል።

ሌላው የእነሱ ድርጅት አመራር አባል ኤፍሬም ሌጀቦ ነው። አዋሳ ተወልዶ ያደገ፣ በቀይ ሽብር ጊዜ መኢሶን ሆኖ ከሌላው ወልደዮሐንስ ይባል ከነበረ ሰው ጋር፣ በመቶ አለቃ ተክሌ ትዕዛዝ ብዙ የሕዝብ ልጆችን የመተረ ነው። ከቅርብ ቀናት ወዲህ በጋሪያቸው የተሳፈረው ሌላው ሰው ደግሞ ዶክተር ጌታቸው በጋሻው ነው። ትግሉ እየመረረ ሲመጣ፣ ለአንድነት ለእኩልነት ሲፋለሙ የወደቁ ጓዶቹን አደራ ክዶ፣ 'ሞት ለኢህአፓ!' ብሎ መፈክር በማርገድ፣ ድርጅቱን ለማጥፋት የሞከረ በታኝ ነው። ድርጅቱ መልሶ ሲያስገባውም፣ በቅርቡ ዳግም አንጃ ፈጥሮ ወጥቷል።

እነኝህ ሰዎች በአንድነት ስም አንድነትን ገድለውላቸው፣ ኢትዮጵያን በዘር ቅርጫ ለመቀራመት ከተዘጋጁት የዘር ድርጅቶቸ መሪዎቸ ውስጥ አንዳንዶቹ በተለይም የኦነጎቹ በመኢሶን አባልነት ከእነኤፍሬም ሌጀቦ ጋር በሕዝብ ልጆች ደም እጃቸውን የታጠቡ ናቸው። የኦብነግም ቢሆን መሪው የዚያድ ባሬ የጦር መኮንን ነበር። የበታቾቹና አባላቱም ምን ያህሉ ኢትዮጵያዊያን እንደሆኑ ለክርስቲያኑ እግዜር፣ ለእስላሙ አላህ ይወቀው። ይህም በባእድ ከሚመራ ድርጅት ጋር ለስንት ዘመናት ደምና አጥንት እየተከፈለ ተጠብቆ በቆዬ የሀገር ህልውና ላይ የነብርሀኑ ድርጅት ማን የመደራደር ስልጣን እንደሰጠው ሌላ ጥያቄ ያጭራል። ብቻ ይህ የሰሞኑ የዘር አሸሸ ገዳሜያቸው ብዙ ብዙ ጥያቄዎቸን እንዳረገዘ ልብ ሊሉት ይገባል። መሪዎቹም ጉዳዮችን አድበስብሶ ለማለፍ፣ እንደውም ለመቅጠፍ ወደሁዋላ እንደማይሉ በገሃድ አሳይቷል።

1. በቅድሚያ "በኦነግ አመራር መካከል የኢትዮጵያ አንድነትን በመቀበል/ባለመቀበል ጥያቄ ላይ ልዩነት ተፈጥሮ ተከፋፍለዋል" የሚሉት ውሸት ነው። በድርጅቱ ስም የተከፈቱ ሁለት ድረ-ገፆች እንደሚያትቱት የትግላቸው ዓላማ ”ከአብስኒያ ቅኝ አገዛዝ ነፃ መውጣት" ነው። ለማስረጃም ፅሁፋቸው እንደወረደ እነሆ፡

“The Oromo Liberation Front (OLF) is a political organization established in 1973 by Oromo nationalists to lead the national liberation struggle of the Oromo people against the Abyssinian colonial rule. The emergence of the OLF was a culmination of a century old yearn of the Oromo people to have a strong and unified national organization to lead the struggle. … OLF's commitment to this objective is based on a democratic principle, that the Oromo people are endowed with the right to decide the type of sovereignty they want to live under and the type of political union they want to form with other peoples ”

(http://www.oromoliberationfront.org/OLFMission.htm)

The Oromo Liberation Front [OLF] is a political organization that is struggling for the realization of the national self-determination for the Oromo people and establishment of independent state of Oromia. Before the Oromo people were conquered by Abyssinia toward the last decades of the 19th century, they lived under an independent democratic political system, known as the Gadaa system. Ever since the conquest, the people are subjected to different forms of domination by successive rulers of Abyssinia, which later took the name Ethiopia.

http://www.oromoliberationfront.info/objectives.htm

2. የግንቦት 7 ሰዎች በተለይም ብርሃኑና አንዳርጋቸው በየጊዜው በትብብር በሚያዘጋጇቸው ሕዝባዊ ስብሰባዎች ላይ ኦነግም ሆነ ኦብነግ በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ሥር ጥያቄዎቻቸውን ለመነጋገር ፈቃደኛ ናቸው ቢሉንም የተጠቀሱትን ድርጅቶች እየወከሉ ከየጎናቸው የተቀመጡት አመራሮች የሚነግሩን ተቃራኒውን ነው። በኤርትራው ዓይነት የፌዝ ሕዝበ-ውሳኔ (ሪፈረንደም) የመገንጠል ጥያቄያችንን እናስወስናለን ነው የሚሉን።

3. ዶ/ር ብርሃኑ በቅርቡ የእነኝሁን እንገንጠል ባዮች ጥያቄ ተገቢነት ለማስረገጥ/ለማሳመን "<u>የዜግነት መብቶች ካልተከበሩ፣ የኢትዮጵያዊነት ብያኔ/ትርጓሜ አከራካሪና ዋጋ የለሽ እንደሆነ የሰበከው</u> የሚያስተዛዝብ ነው። ከክትፎ፣ ቆጮ መውደድ ተነሥቶ የእንግሊዙን እግር ኳስ ቡድኖች አርሰናልንና ማንችስተር ዩናይትድን እስከመደገፍ ያሉ ግልሰባዊ ምርጫዎችን በምሳሌነት በማጣቀስ የ"ኢትዮጵያዊነት"ን አሰባሳቢነት ትርጉም የለሽ ለማድረግ መጣሩ "አሁንስ በዛ!" ያሰኛል። ኢትዮጵያዊ ናችሁ ብሎ ጠርቷቸው ለመጡለት ታዳሚዎች፣ በኢትዮጵያዊነታቸው ለሚያምኑት አባላታቸውም ስድብ ነው። በእዚህ አመክንዮ/ተጠየቅ ከሄድንም በዚህ ምድር ላይ ሀገራት አይደሉም፣ ትንንሾቹ የጋራ እሴቶች መገለጫ የሆኑ መሰባሰቢያዎችም ህልው ሆነው ባላየን። መቼም የትም ሀገርም ሕዝብ የዜግነት መብቴ አልተከበረልኝም ብሎ፣ በራሱ ሀገር ላይ የቄራ ውሻ ሆኖ፣ ሀገሩንም የአህያ እሬሳ አድርጎ በራሱ ፈቃድ ሲቧጩቅ አልተስተዋለም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል ታሪክም የሚያስረግጠው ይህንኑ ነው። ከቅርቡ ብንጀምር እንኳ ጣሊያን ወረራ ስታካሂድ ከሠሜን፤ ከደቡብ፣ ከምዕራብ፣ ከምሥራቅ ክተት ብሎ በአንድነት ለጋራ ነፃነቱ ተዋጋ እንጅ ቢበታተንማ ኖሮ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር በጊዜያችን ባልኖረች፣ እሁም ስለዚችው ሀገር ባላወራ ነበር። በ1997 ምርጫ ወቅትም እሱ አመራር የነበረበትን ቅንጅትን እና ህብረትን ብዙሃኑ ህዝብ ባልመረጠ ነበር። ከመናገር በፊት፣ ምን ይሉኝን ማሰብ ከትዝብት ያድናል።

ይቀጥላል።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!
ክብር ለአንዷት ኢትዮጵያ ሠማዕታት!